## ፓኖራማ ቁጥር 47

## የትዝብት አድማስ

**ጥቅምት 14 ቀን 2001 ዓም**

### ነጋዴው ሥርዓት

አንድን ንዑስ የሀገሪቱ ክፍል ከሌላው የኢትዮጵያ ሰፊ መልክዐ-ምድር በመለየት የሪፑብሊክ መንግሥት በመመሥረት ብቻዋን አለማለሁ ብሎ የተነሳው ወያኔ÷ ሰኔና ሰኞ ስለገጠሙለት ይኸው ዛሬ ማስገንጠሉን ለጊዜው ያቆመ በመምሰል ቢያደፍጥም÷ የተነሳበትን ሌላውን ዓላማ በማሳካት ላይ ግን ይገኛል፡፡ እንኳን ተመልካችን ቀርቶ እራሱ ወያኔንም ሳይቀር በሚያስገርመው ፍጥነትና ስፋት የተነሳበትን አካባቢ በሁለንተናዊ መልኩ እያለማ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያ በየጊዜው ከውጭ ጠላቶቿ ጋር ባደረገቻቸው ተደጋጋሚ ጦርነቶች የመጀመሪያውን የጦር ገፈታ በመቅመስና አሳዳውንም በመጋፈጥ ግንባር ቀደም ሚና ስትጫወት የነበረችው ኢትዮጵያዊት የትግራይ መሬት እንደነበረች አንድና ሁለት የለውም፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ የሚደረግላት የልማት ዕድገት አይበዛባትም፡፡ በሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በኩልም የትግራይ ሕዝብ ለምን የልማት ዕድል ገጠመው ብሎ ቅር የሚለው አይሆንም፡፡ መሠረታዊው ጥያቄ ግን ይህ አይደለም፡፡ ከዚህ የበለጠና የዘለለ ነው፡፡

ኢትዮጵያን አስተዳድራለሁ የሚለው ወያኔ የጠባብ ባሕርዩና ሰብዕናው ምንጊዜም ስለማይለቀው÷ እጅግ አሳፋሪ በሆነ አድልዎ የተከበረውን የኢትዮጵያ መንበረ-መንግሥት እያዋረደና ቀሪውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ንቆና ጠልቶ የሚያደርገው ወራዳ አድላዊ ተግባሩ ነው ክፋቱ፡፡ ይህ አስነዋሪና አስተዛዛቢ ተግባሩ ነው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያሳዝነው፡፡ በኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ ዘመን የመንግሥት ታሪክ ሂደት ከመንበረ-መንግሥት ሥልጣን ተቀምጦ የነጋዴ ሥራ በማጧጧፍ ወያኔ የመጀመሪያውን ክበረ-ወሰን ይዟል፡፡ የወያኔ የነጋዴ ተግባሩ የኢትዮጵያን አካል ገንጥሎ ከመሸጥ ጀምሮ የጦር መርከቦችንና የጦር አይሮፕላኖችን በሀራጅ እስከመቸብቸብ ድረስ ያለውን ያጠቃልላል፡፡ የወያኔ ንግድ ሥራና እንቅስቃሴ÷ የመላ ሀገሪቱን የኢኮኖሚ አውታር ስለተቆጣጠረው የወያኔ "መንግሥት"ና የወያኔ የችርቻሮ ሥራ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆነዋል፡፡ የአስመጭና ላኪውን÷ የባንክንና የኢንሹራንሱን÷ የማጓጓዣንና የማከፋፈያውን÷ የአገልግሎት÷ ሰጭውን÷ የሕንፃ ሥራውንና የታላላቅ ኮንትራት ተቋራጭነቱን÷ የጅምላውንና የችርቻሮውን አካትቶ እስከ ጉልት ገበያ ያለውን ጥቃቅን የገንዘብ ማስገኛ ቦታዎችን ሳይቀር በስግብግብነት ወስዶ ይጠቀማል፤ ይቆጣጠራል፡፡ የሚያሳዝነውና ሲሰሙትም የሚያሳፍረው÷ ይህንን ሁሉ የስግብግብነት አስነዋሪ ሥራ የሚፈጽመው ወያኔ÷ በኩሩውና በተከበረው የትግራይ ሕዝብ

ስም መሆኑ ነው:: ጉዳዩ÷ “ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል” ዓይነት ነገር ሆኗል:: በኢትዮጵያ ታሪክና ባሕል መሠረት÷ መንግሥት የተሰኘው ተቋም÷ ጨቋኝም ይሁን የተጠላ÷ በሕዝቡ ዘንድ ግን ሁልጊዜ የተፈራና የተከበረ ነበር:: መንግሥት የሕዝቡን ፍራቻና ከበሬታ የሚያተርፈው ግን ቢያንስ በአንድ መሠረታዊ ጉዳይ ብቻ ነበር:: ይኸውም መንግሥታዊ ተቋሙንና መንበረ መንግሥቱን እንደ ወያኔ የሚያዋርድና የሚያሳፍር ሥራ ስለማይፈጽም ብቻ ነበር:: መንግሥታዊ ተቋሙ የሚፈራው በኃይሉ÷ የሚከበረው ደግሞ በመንበሩ ላይ የተቀመጠው እራሱን አስከብሮ ተቋሙን ማለትም መንበረ-መንግሥቱን ስለሚያስከብር ብቻ ነበር:: እዚህ ላይ በመሠረቱ አንድ ነገር ግልፅ መሆን አለበት ብለን እንገምታለን:: ይኸውም÷ ምንም እንኳን ከባኅላዊ እሴት አኳያ ሲታይ÷ በሀገራችን መንግሥት የሚባለው ተቋም ባይወደድና ባይታመንም ቅሉ÷በአመዛኙ እንደ ወያኔ የሚያሳፍርና የሚያስንቅ ተግባርና ባኅርይ ስለማያሳይ÷ ባይወደድም የተፈራ÷ ባይናቅም የተከበረ ነበር ለማለት ይቻል ይመስለናል:: በግለሰብም ይሁን በመንግሥት ደረጃ÷ ሰው ራሱንም ሆነ ተቋሙን አክብሮ ካላስከበረ ማንም አያከብረውም:: የወያኔ ሰዎች እራሳቸውንም ሆነ ድርጅታቸውን እነርሱ እራሳቸው ስላዋረዱት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የተናቁና የተጠሉ ናቸው:: አሁን ደግሞ ከአለፈው 97 ዓም የግንቦቱ የወያኔ ምርጫ በኋላ ተደፍረዋል:: ተንቀዋል:: ተዋርደዋልም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በነእርሱ ላይ ያለውን የከረረ ጥላቻ ለመረዳት እያንዳንዱን ዜጋ መጠየቅ ብቻ በቂ ነው:: ይህንንም እነርሱ ራሳቸው ወያኔዎቹ ጠንቅቀው ያውቁታል:: ቢያንስ ይህንን ለመገንዘብ መሰሪነታቸው ይፈቅድላቸዋልና:: ለዚህም ነው የወያኔ መሪዎች በአሁኑ ሰዓት በአሮጌ ግንብ ውስጥ እንደምትቅበዘበዝ ብቸኛ ድንቢጥ በምንሊክ ግቢ ውስጥ እንደ እስረኛ በራሳቸው በጦር መሣሪያ ተከብበው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ተገልለውና ተደይነው የሚኖሩት:: የሰላዩና የወሬ አቀባዩ ሠራዊት ቁጥር በየጊዜ እየጨመረ መሄዱም÷ በዚህ መሠረታዊ ምክንያት ነው:: በሀራችን ታሪክ÷እንደ ወያኔ አዋራጅና አሳፋሪ ተግባር በመንግሥት ስም ተፈጽሞ ስለአልነበር÷ መንግሥት የሚባለው ተቋም ሌላው ቢቀር በተቋምነቱ ብቻ እንኳን የተፈራና የተከበረ ነበር ቢባል÷ ከዕውነት አይርቅም:: የወያኔ “መንግሥት” ግን የተፈራም የተከበረም አይደለም:: በመሠረቱ ወያኔ ሊፈራም ሆነ ሊከበር የመጣ ባለመሆኑ÷ እርሱ ቢጠላ÷ ቢፈራ÷ ቢናቅም ሆነ ቢዋረድ ደንታ አይሰጠውም:: ይህንን ለመረዳት ይሉኝታ የሚባል ሥነባኅርይ እንዲኖር ያስፈልጋል:: በመሠረቱም ቢሆን ወያኔ ከመጀመሪያው አመጣጡ ይሉኝታና ኃፍረትን አንግቦ ስለአልመጣ÷ አንዳንዶቹ እንደሚገረሙት÷ እኛ ወያኔ ለምን ይሉኝታ የለውም የሚል ብዥታ ኖሮን አያውቅም:: ታዲያ ዛሬ እኛ ልናነሳው የፈለግነው ዋናው ጉዳይ÷ ስለ ሕዝብና ስለ መንግሥታዊ ተቋምና ስለ ሚኖራቸው የመርኅ ግንኙነትና ትሥሥር ብቻ ነው:: በኢትዮጵያ የአያሌ ዘመን የመንግሥት ታሪክ÷ እንደ ወያኔ ከከፍተኛው የነጋዴ ተግባር እስከ ጥቃቅን የችርቻሮ ሸቀጥ ውስጥ በመሳተፍ የውርደት ሥራ የፈጸመ መንግሥት እንዳልነበረ ለማስገንዘብ ብቻ ነው:: ቀደምት የኢትዮጵያ መንግሥታት የሀገሪቱን ዳር-ድንበር እያስከበሩ አለፉ እንጅ÷ እንደ ወያኔ አገር ሸጠው ወደ ንግድ ሥራ በመሠማራት መንበረ-መንግሥትን አላዋረዱም:: ምንም ዓይነት

ይዘት፥ ባሕርይና ተግባር ይኑረው፥ በኢትዮጵያ ስም መንግሥት ነኝ ካለ፥ ሌላው ቢቀር የኢትዮጵያን ስም የሚያዋርድ መሆን አይገባውም። ይህንን እንዲያው ለግንዛቤ ያህል ለመጥቀስ ፈለግን እንጅ፥ ወያኔ እንኳንስ ስሟን እራሷን ሀገሪቱን እያጠፋት እንዳለ የታወቀ ነው።

"የአህያ ሥጋ ከአልጋ ሲሉት አፈር" እንደሚባለው፥ ወያኔ የሚያደርገው ይህንኑ ነው። ወያኔ ባይሰማውም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ይህ ተግባር ያሳፍረዋል። የሚያፍረውም በሀገሩና በራሱ ስም የሚፈጸመውን አዋራጅና አንገት ሰባሪ ተግባር በማየቱ ብቻ ነው። ይህንን የወያኔን ዓይን-አውጣ ድርጊት ከታዘበ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን፦

"ነጋዴ ነህ አሉ መንግሥት አይነግድም" ብሎ ቢለው፥ ዓይን-አውጣው ወያኔ "ሂድ ሞኝህን ፈልግ" ካለ በኋላ፥ "ወረቱ ካለቀ ሰው አይወደድም" የሚል መልስ ሰጥቶታል። ከወያኔ ከዚህ የተለየ መልስ አይጠበቅምና መልሱ ሊያስደንቅ አይችልም። ለተከበረ ሀገራዊ ዓላማ ካልቆመ ድርጅት፥ ለሀገርና ለሕዝብ ስትራቴጂያዊ ጥቅም ካልመጣ የጠባብ ብሔረተኛ ቡድን፥ አፈጣጠሩና ዕድገቱ ለመላው ኢትዮጵያ ካልሆነ የሀገር ውስጥ ጠላት፥ ከገንዘብና ከቆሳቁስ የተለየ ሕልም ስለሌለው፥ ወያኔ የሰጠው መልስ ትክክል ነው። አፈጣጠሩና ዕድገቱ ዓላማና ግቡ ኢትዮጵያን እያጠፉ ጠባብ ዓላማውን ከግብ ማድረስ በመሆኑ ለወያኔ መከበር፥ መታፈር፥ መፈራትና መወደድ ደንታ አይሰጠውም። ታሪክን ለማጥፋት እንጅ ታሪክን ለመሥራት ባለመምጣቱ ታሪኩ ቢበላሽ ባይበላሽ ወያኔ ጉዳዩ አይደለም።

በአገር ቤት ያለውን የንግድና የፋይናንስ ምንጩን ከተቆጣጠረ በኋላ በአሁኑ ሰዓት ነጋዴው ወያኔ የንግዱን አድማስ በማስፋት በውጭ ሀገርም በተለያዩ ባንኮችና የፋይናንስ ማዕከሎች በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እያስቀመጠ (ኢንቬስት በማድረግ ላይ) ይገኛል። በሎንደን፥ በጄኔቫና በኒዮርክ በፓሪስ በሮማና በሌሎቹም የአውሮፓ ታላላቅ ከተሞች በሚገኙ ታላላቅ ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማትና የገንዘብ ማዕከሎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብትና ንብረት እየተዘረፈ ይከማቻል። በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ከዓለም ገንዘብ አበዳሪ ተቋማት እየተወሰደ ገንዘቡ የፈረንጆቹን ባንኮችና የንግድ ማዕከሎች ትርፍ ማስገኛ ምንጭ ይሆናል።

ይግረማችሁ ብሎም፥ይህ የወያኔ ድርጅት፥ በሀገር ውስጥ የሚገኙትን ማነኛውንም የገንዘብ ተቋማትና የትርፍ ማግኛ ድርጅቶችን በሁለንተናዊው መልኩ በመዳፉ ካስገባ  በኋላ፥ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የዓለም ሀገሮች ወኪሎቹን በመላክ፥ ከወያኔ ተባርረው የወጡት ኢትዮጵያውያን ስደተኞች የሚተዳደሩበትን የንንግድ ተግባር በመሻማት ላይ ይገኛሉ። በተለይ ይህ ድርጊት በሰፊው የተከሰተው በሰሜን አሜሪካ ከተሞች እንደ ዴንቨር ኮሎራዶ፥ ኮሎምቦስ ኦሃዮ፥ ዋሽንግቶን ዲሲ፥ ዳላስ ቴክሳስ፥ ችካጎ ኢሊኖይ፥ ባሉና በሌሎቹም የዩናይትድ ስቴትስ ከተሞችና ግዛቶች መሆኑ ተደርሶበታል። ይህ  ሰፊ ዕቅድና ቅንብር የተመላበት የወያኔ ድርጊት፥ ለጊዜው ተከላለካይ ያጣችውን ጥገቱን  ኢትዮጵያን አልቦ አልቦ ከነጠፈችለት በኋላ፥ ጊዜው

*ሲደርስ፥ ጥሏት እንደሚኮበልል ስለሚያውቀው፥ ከአሁኑ መገልበጫውን ለማዘጋጀት እንደሆነ ለማንም የተሰወረ ሊሆን አይችልም። ይህን ለመገመት ደግሞ ሊቀ ጠበብት መሆንን አይጠይቅም።*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ በግፍና ሕገወጥ በሆነ መንገድ የሚዘረፈውን ሀብቱን ወደፊት በሆነው መንገድ የማስመለስ ሕጋዊ መብቱ እንደተጠበቀ ቢሆንም፥ በአሁኑ ወቅት ግን ቅድሚያ የሚሰጠው ከዚህ ዘራፊና ነጋዴ የብሔር ድርጅት አምባገነን አገዛዝ ሥር ለመላቀቅ መታገልን ብቻ ነው። ሕዝባችን በእርግጥም ዛሬ የቅድሚያ አጀንዳው የተዘረፈውን ሀብት ማስመለስ ሳይሆን፥ ዘራፊውን ማስወገድ ነው። ዘራፊውን የነጋዴዎች ድርጅት ለማስወገድ ነው። ዘራፊውን የነጋዴዎች ድርጅት ለማስወገድ ደግሞ ያለው አማራጭ በግድ ተባብሮ በጠነከረ ክንድ መታገል ብቻ ነው። ያ እስካልሆነ ድረስ ዝርፊያው ይቀጥላል። ዘራፊው ነጋዴ ወያኔም የሀገሪቱን ሀብት ማሟጠጡን በገፍ ያካሂዳል። ቤትን ሳይዘጉ ቀርተው፥ ዘራፊን ቢያማርሩት ትርፉ፥ የዘራፊው መሳቂያ መሳለቂያ መሆን ብቻ ነው። በዕርግጥም ይህ ዘራፊ ነጋዴ የወያኔ ቡድን መወገድ አለበት። ያለዚያ፥ "ዝም በሉ! ወያኔ ያልፋል።" እየተባባሉ እራስን ቢደልሉ፥ እስኪያልፍ የሚያለፋ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ነጋዴና የመንግሥት ሥልጣን ከተዋሃዱ ደግሞ ፥እስኪያልፉ ድረስ ዝርፊያውን እንደሚቀጥሉ መረዳት አስፈላጊ ነው።*